# ክርክሩ ከጥሩ ሥነ-ምግባር ጋር

ቻላቸው Chebudie@yahoo.com

ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ምርጫ የሕዝቦችን ሕገ-መንግሥታዊ የሥልጣን ባለቤትነት በማረጋገጥ ጠንካራ መሠረት ያለው ሕዝባዊ መንግሥት በመገንባት ረገድ ዓቢይ ሚና ይጫወታል፡፡

የመምረጥ መብቱን ያልተጠቀመና ያገለግሉኛል ብሎ ድምፁን ሰጥቶ ያልመረጣቸው መሪዎች የአስተዳደር በደል ቢያደርሱበትና ብልሹ አሰራር ቢሰፍን ምንም እንኳን ሕዝቡ በማንኛውም ጊዜ አመራሩን የመጠየቅ መብት እንዳለው ቢታወቅም በመረጠው አካል አለመተዳደሩ በራሱ የዴሞክራሲን መርህ ይፃረራል፡፡ በምርጫ መሳተፍ የዜጎች መብት ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትም ጭምር ነው፡፡ ሕዝቡ ካልመረጠና ካልተመረጠ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረቱ እንዲጠናከርና እንዲጎለብት የዜጎች ቀጥተኛ ተሳትፎና ጥረት መኖር የግድ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የዴሞክራሲን መሠረት ለመጣል እንደማይቻል በተግባር የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አገራችን ዛሬ ለምትገኝበት ድህነትና ኋላቀርነት አንዱና ዋነኛው ምክንያት ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በኃይል የተካሄዱት የሥልጣን ሽግግሮችን ተከትለው የተከሰቱት የእርስ በእርስ ጦርነቶችና የሕዝብ ተቀባይነትና ይሁንታን ያላገኙ ገዥዎች በሥልጣን ላይ የዕድሜ ልክ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ ሆነው መቆየታቸው መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

አንድን ምርጫ ነፃ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ከጅማሬው አንስቶ የምርጫ ሂደቱ የተቃና እንዲሆን መራጩ ድምፁን ሰጥቶ ውጤቱ እስኪገለጽ በትዕግሥትና በጨዋነት መንፈስ መጠባበቅ ይኖርበታል፡፡ ከቅድመ ምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር አንስቶ እስከ አጠቃላይ የመጨረሻው ውጤት ድረስ

ሁሉም ሂደቶች የራሳቸው የሆነ አስተዋፅዖ አላቸው፡፡ በተለይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ማን ምን እንደያዘ የሚያሳውቁበትና ልዩነታቸውን ለማሳየት የሚከራከሩበት የክርክር መድረክ በቅድመ ምርጫ ከሚደረጉ ክንውኖች ትልቁን ሥፍራ ይይዛል፡፡ የምርጫ የክርክር መድረክ መኖሩ የሥልጣን ባለቤት ለሆነው ሕዝብ ታላቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ መራጩ ሕዝብ ድምፁን ለማን መስጠት እንዳለበት የሚረዳበትና የሚወስንበት ዕድል ያገኛል፡፡ በክርክር ወቅት የሚቀርቡ የተለያዩ አማራጮችን በማየት በጭፍንና ያለ ዕውቀት ድምፅ መስጠትን በማስቀረት የሚበጀውን በጥንቃቄ መምረጥ የሚያስችለውን ዕድል ይፈጥርለታል፡፡

የዳበረ የዴሞክራሲ ሥርዓት የገነቡና በመገንባት ላይ በሚገኙ አገሮች ይዘቱ ይለያይ እንጂ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር ያደርጋሉ። ኢትዮጵያም ሕገ-መንግሥታዊ ምርጫዎችን ማድረግ ከጀመረች በኋላ በተካሄዱት ሦስት አገራዊና ክልላዊ ምርጫዎች በይዘታቸውና በክብደታቸው የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክሮች ተካሂደዋል፡፡ይህም ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ወኪሉን እንዲመርጥ የራሱን አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይታወሳል፡፡ ይህ የሚያሳየው በአገራችን የተፈጠረውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ማበብ በመጠቀም ሕዝቡ ሕገ-መንግሥቱ የሰጠውን መብት ተጠቅሞ የሚያስተዳድሩትን መምረጥ እንደሚችል የተረዳበት ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ነው፡፡ ምንም እንኳ አንዳንድ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ የሚከተሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባይጠፉም፡፡

ምርጫን ሙሉ ነው ከሚያስብሉት ጉዳዮች ማለትም የቅድመ ምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክሮች፣ የሚዲያ አጠቃቀም፣ የመራጭና የተመራጭ የምዝገባ ሂደትና የምርጫ አስፈጻሚዎች የየራሳቸው የሆነ ቀላል የማይባል ተፅዕኖ አላቸው፡፡ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ሰላማዊ እንዲሆን ደግሞ ሰላማዊ የሆነ የቅድመ ምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር ወሳኝነት አለው፡፡

በ2002 ግንቦት ወር ለሚካሄደው ምርጫ የመጀመሪያው የፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡን ዘመቻ ክርክር ሰሞኑን ተካሂዷል፡፡ #መድብለ ፓርቲ፣ ምርጫና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ; በሚል ርዕስ፡፡ ኢህአዴግ፣ ኤዴፓ፣ ቅንጅት፣ የኢትዮጵያ

ራዕይ ፓርቲ፣ ኢ.ፍ.ዴ.ሃግና መድረክ በዚሁ የመጀመሪያ የክርክር መድረክ ተሳትፈዋል፡፡

አሃዱ በተባለው በዚሁ የፓርቲዎች ክርክር የተለያዩ ሃሣቦች ከሁሉም ፓርቲዎች ተነስተዋል፡፡ በዚሁ የክርክር መድረክ አንድም የተቃዋሚ ፓርቲ ለህዝቡ ይዞ የቀረበውን ፖሊሲ፣ስትራቴጂና ፕሮግራሙን ሲያቀርብ አልተስተዋለም ፡፡

በተጨማሪም በዚህ የምርጫ ውድድር ውስጥ የተስተዋሉትን ክስተቶች በጥቂቱም ቢሆን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የምረጡኝ ቅስቀሳው የተጀመረው በብዙ አገሮች የሚሰራበትን የውድድር ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከ97ቱ የምረጡኝ ቅስቀሳ ጋር ሲነፃፀር በዴሞክራሲያዊነቱ የተሻለ እንደሆነ ከገዥው ፓርቲም ሆነ ከተቃዋሚ ፓርቲዎችም አቀራረብ መረዳት ይቻላል፡፡ በ97ቱ ምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ከመጀመሪያው አንስቶ በጭፍን የመቃወም ሁኔታ የተስተዋለበት ነበር፡፡ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች በፓርላማ ውስጥ እያሉ የነበረውና በአሁኑ ክርክር የተናገሩት ነገር ግራ አጋብቶኛል። ፓርላማ ውስጥ እያሉ ቢያንስ በጥቂቱም ቢሆን ሀገሪቱ እያስመዘገበች ያለችውን የልማት እንቅስቃሴ መልካም መሆኑን ሲናገሩ ነበር። በተለይ ኤዴፓ በገዥው ፓርቲ በኩል የተከናወኑ ሥራዎችን ከመደገፍ ጀምሮ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ የሚከተሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እስከመታገል ሲሞክሩ ተመልክተን የሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት እየተሻሻለ መጥቷል አስኝቶን ነበር። ኢ.ዴ.ፓ ዛሬ ምን እንደተገኘ ባይታወቅም ስንት የአገራችንን አንጡራ ሃብትና የዜጎችን ጉልበት በከባድ ሁኔታ የፈተነውን፣ ሃገራችን ታላቅ ተስፋ የጣለችባቸውን ታላላቅ ፕሮጀክቶች #ሲሚንቶ ተቦክቶ የተሰራ ልማት ልማት ሊባል አይችልም; ማለታቸው በጣም ያሳዝናል፡፡ በአዲስ አበባና በሌሎች የክልል ከተሞች የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምንም ዋጋ የላቸውም ማለት ነው? የተለያዩ የሃይል ማመንጫ ተቋማትስ? ልማት እንዲባሉ የግድ በወርቅ መሰራት ነበረባቸው እንዴ?

ተቃዋሚዎች በጭፍን መቃወምን አስወግደው የተሰሩ ወይም የተመዘገቡ ልማቶችን በማድነቅ የሚታዩ ግድፈቶችን ለሕዝብ በማሳየትና ከሌሎች የሚሻሉበትን

ህብረተሰቡ እንዲገነዘብላቸው ቢያደርጉ የበለጠ የዴሞክራሲ መሠረት መጣል እንደሚቻል ሊታመን ይገባል፡፡

በክርክሩ ወቅት መረዳት እንደቻልኩት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የያዙትን ፍልስፍና በጥቂቱም ቢሆን ለመግለፅ ከመሞከር ውጪ ዝርዝር የሆነ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፈው ሕዝብ አማራጭ እንዲኖረው የሚያስችል ፕሮግራም አቅርበዋል ማለት አልችልም፡፡ ምናልባት ወደፊት በሚደረገው ክርክር ተቃዋሚዎች ከገዥው ፓርቲ በምን መልኩ እንደሚሻሉና ወደ ተግባር ሲለወጥ ውጤታማ ሊሆን የሚችል ፖሊሲ እና የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ አጀንዳዎችን አቅርቦ ለሕዝብ ሲያስረዳ ነው፡፡ ሕዝቡ አማራጩን አይቶ ድምፅ ሊሰጠው የሚችለው፡፡

ነገር ግን እየታያ ያለው ተጨባጭ የፖሊሲ አማራጮችን ከማምጣትና የራስ የሆነ አቋምን ከማራመድ ይልቅ ዘለፋና ጨዋነት የጎደለው ንግግርን እያስደመጡን ይገኛሉ አንዳንድ በክርክሩ የተሳተፉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች፡፡ በልማት፣ በሰላም፣ በመልካም አስተዳደር፣ በዴሞክራሲና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የራስ የሆነ ፕሮግራምን ማቅረብና ሕዝቡ ግንዛቤ እንዲኖረው አለማስቻል በክርክር ወቅት ላልተፈለገ ንትርክና ጨዋነት ለጎደለው ንግግር መጋበዙ አይቀርም፡፡

መድረክን ወክለው ከተከራከሩት ከዶክተር መረራ ጉዲና የተሰማው የመከራከሪያ ነጥብ  ደግሞ በጣም አስገርሞኛል። ሁሌም የዚምባብዌንና የኬንያን ሁኔታ በማንሳት እኛም የግድ ያለቀው ይለቅ ሥልጣን ላይ መውጣት አለብን የሚል ዝማሬ ዛሬም ድረስ እያቀረቡልን ይገኛሉ፡፡ በአስከፊነቱ እና ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ዳግም አይመልስህ ተብሎ በዜጎቹ የተረገመው የዚምባቡዌንና የኬንያ ምርጫ ተሞክሮ በኢትዮጵያ እንዲመጣ የዘወትር የነ ዶክተር መራራ ፀሎት ሆኗል።

መድረኮች ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያን ማስተዳደር ከተፈለገ ብዙ መፃሕፍትን ማንበብ ተገቢ ነው የሚል ምክርም በክርክሩ ወቅት አስደምጠውናል፡፡ በእርግጥ ብዙ መፃሕፍትን ማንበብ በትምህርት ቤትም ይሁን በሌላ ቦታ ሊነሱ የሚችሉ

የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይረዳል፡፡ አገርን ለማስተዳደርም እንዲሁ፡፡ መመልከት ያለብን ጉዳይ ግን ሺህ መፃሕፍት ቢነበቡ ለአገር በሚጠቅም መልኩ ተጨምቀው ካልተተገበሩ ተነበቡ ሳይሆን ተሸመደዱ ይሆናል፡፡

የዶክተር መረራ ሌላ ድራማ ደግሞ ምን እንደሚመስል ከገዥው ፓርቲ በኩል ሲነገር ተሰምቷል፡፡ ሁሌም አባሎቼ ታሰሩ በማለት በየመድረኩ የሚያነሱ አንድም ሌላ ወንጀል ሰርቶ የታሰረን ግለሰብ የእኔ አባል ነው ለማለት እንዲያስችላቸው ማረሚያ ቤት ድረስ በመሄድ የአባልነት መታወቂያ አሰርተው እንደሚሰጡ ነው የተረዳሁት፡፡ ይህ ድርጊት በእውነቱ በጣም አሳፋሪ ነው፡ ከኢህአዴግ በኩል ይህ ብቻ አልነበረም የተሰነዘረው፡፡ በይፋ በየጋዜጣው ላይ  #እኔ ካላሸነፍኩ ምርጫው ተጭበርብሯል፣ ኮሮጆ ተሰርቋል; የሚል የፖለቲካ አመራር በውስጣችሁ ይዛችሁ ገዥውን ፓርቲ ትኮንናላችሁ የሚል ሃሣብም በክርክር ወቅት ተነስቷል፡፡ እርግጥ ነው አንድ ፓርቲ ወደ ምርጫ ውድድር ሲገባ የማሸነፍ ወኔ ሰንቆ መነሳቱ አግባብነት ያለው ቢሆንም መዘንጋት የሌለበት ግን የሥልጣን ባለቤት የሆነው ሕዝብ በድምፁ የሰጠውን ሥልጣን ተጠቅሞ እንጂ በምንም ዓይነት ተአምር ወደ ሥልጣን ሊመጣ አይችልም፡፡ ሕገ-መንግሥቱ የሰጠውን መብት ተጠቅሞ በምስጢር ድምፅ የሚሰጥ ሕዝብ እስከሆነ ድረስ ሥልጣን መያዝ የሚቻለውም በዚህ ድምፅ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡

ዶክተር መረራ ከኢህአዴግ በኩል ኦነግን አስመልክቶ በተነሳው ሃሣብ ላይ መልስ ሲሰጡ ኦነግን እየቀለበ ያለው ኢህአዴግ እንደሆነ የተናገሩት ጉዳይ እጅጉን ገርሞኛል፡፡ ዶክተር መረራ ከኦነግ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌላቸውም ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡ ከኢህአዴግ በኩል የተሰጠው ሃሣብ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም አንድን ቡድን ወይም አካል ከፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄዱ እንዲመለስ የማሳመን ተግባርሥራ በማከናወን መስራት ወደሰላማዊ ትግል ማምጣት ይገባል እንጂ  እያደኑ መግደል መቼም አይደገፍም፡፡ ከሥርዓት አልበኝነት በመፀፀት የሚመለስን ማንኛውንም ወገን ቢሆን ወደሥርዓቱ አስገብቶ የልማት አጋር ማድረግ ብልህነት ይመስለኛል፡፡

ከኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ በኩል የተነሳውን ሃሣብ ብንመለከት የተቃዋሚዎች መኖር ለኢህአዴግ ጥሩ ነው፡፡ ኢህአዴግ ጠንክሮ እንዲሰራ ያደረገው የቀድሞው ቅንጅት እንደሆነ እና አሁንም የተቃዋሚዎችን መኖር አጥብቆ ሊቀበለው ይገባል ዓይነት ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የተለያዩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖራቸው የተለያዩ ሃሣቦችን በማፍለቅ ለሀገር በሚጠቅም መልኩ ማቅረብ ሲችሉ መሆኑን ሁላችንም ያስማማናል፡፡ እንዲያው በደፈናው ተቃዋሚዎች በቁጥር ስለበዙ ብቻም ጥቅም አለው ማለትም አይደለም ብሎ ተቃዋሚ የገኙ ፓርቲን ችግሮች ነቅሶ ማሳየት ጥሩ ነገር ቢሆንም ሥርዓት በሌለው መንገድ መሆን የለበትም፡፡ የልማት እንቅስቃሴውን ያደነቁበትን ያህል በፀረ-ዴሞክራሲያዊ መንገድ ሥልጣን የሚሹ ፓርቲዎችን ልክ እንደ ኢ.ዴ.ፓ. ሁሉም ተቃዋሚዎች ሊቃወሙት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩን መንፈስ ስንመለከተው በአንድ መልኩ የቃላት ጦርነት የታየበት በሌላ በኩል በመግባባትና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ክርክር የተካሄደበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ቀጣይ በሚደረጉት ክርክሮች የራስ የሆነን ፕሮግራም በግልጽና በማያሻማ መልኩ ማቅረብ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ለሕዝብ አማራጭ ፖሊሲን ሳይዙ ወደ ክርክር መግባት ለስሜት ስለሚዳርግ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ምርጫ በአገራችን ይካሄድ ዘንድ አኩሪ ፉክክርና ክርክር ከጥሩ ሥነ-ምግባር ጋር ያስፈልጋል እላለሁ፡፡ቸር እንሰንብት!